በመንጃ ፈቃድ ወይም በመታወቂያ ካርድ ላይ የጾታ ስያሜ

በመንጃ ፈቃድ ወይም በመታወቂያ ካርድ ላይ ያለ የጾታ ስያሜ ለመቀየር የሚደረግ የአሰራር ሂደት

የማንነታቸው ማረጋገጫ መረጃዎቻቸው ላይ ከሚታየው የጾታ ስያሜ በመንጃ ፈቃዳቸው ወይም የመታወቂያ ካርዳቸው ላይ እንዲቀየር የሚጠይቁ አመልካቾች፤ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ሟሟላት አለባቸው፡-

- ማንኛውንም ወቅታዊ በስቴት የተሰጠ የመንጃ ፈቃድ ወይም የመታወቂያ ካርድ ማስረከብ፤
- የተሞላ የጾታ ስያሜ ቅጽ (Gender Designation form)፤ እና
- ለአዲስ ወይም ተሻሽሎ ለሚሰጥ መንጃ ፈቃድ ተገቢውን ክፍያ መክፈል። አመልካቹ/ቿ አዲስ ፎቶ መነሳት ይኖርባቸዋል።

ሰራተኞች ሕጋዊ በሆኑት ቅጾች ላይ ከሚጠየቁት በላይ ተጨማሪ ጾታ-ነክ መረጃ ወይም የአመልካቹን የግል የህክምና ታሪክ ወይም መዝገቦችን መጠየቅ የለባቸውም።

የሞተር ተሽከርካሪ መምሪያ (Department of Motor Vehicles) በዚህ ሂደት ላይ ለሁሉም ሰራተኞች አጠቃላይ ሥልጠና መስጠት እስከሚችል ድረስ የጾታ ስያሜ ማመልከቻዎች በቀጥታ ወደ DMV የአገልግሎት ማዕከል አስተዳዳሪዎች መመራት ይኖርባቸዋል።

ከፆታ ስያሜ ጋር የተያያዘ የመረጃ ምስጢር ጥበቃ

የጾታ ስያሜ ቅጹ የግላዊ ሕክምና መረጃ የያዘ ስለሆነ፤ ምስጢራዊ ሆኖ የሚያዝ እና በአሽከርካሪዎች የግል ምስጢር የሕግ መጠበቂያ ድንጋጌዎች ስር የሚጠበቅ ይሆናል።

ከሌሎች ምንጮች የሚገኙ የጾታ መረጃዎችን ማዘመድ

ዲ.ኤም.ቪ (DMV) ሙሉ በሙሉ እና በትክክለኛ ሁኔታ የተሞላ የጾታ ስያሜ ቅጽን በመመርኮዝ የጾታ ስያሜውን በአመልካች መንጃ ፈቃድ ወይም የመታወቂያ ካርድ ላይ ይቀይራል።አመልካቹ/ቿ የጾታ ስያሜውን ወይም ስያሜዋን በሌላ የመታወቂያ ዓይነቶች ላይ የመቀየር ግዴታ የለበትም/ባትም።

የስም ለውጥ

ከፆታ ጋር የተያያዙ የስም ለውጦች የሚጠናቀቁት ተገቢ የፍርድ ቤት መረጃዎች በማቅረብ ሲሆን እንዲሁም በሶሻል ሴኩሪቲ ካርድ ላይም መቀየር ይኖርበታል።

የጾታ ስያሜ ቅጽ

ክፍል አንድ፡- በአመልካች የሚሞላ

የመጨረሻ ስም	የመጀመሪያ ስም	መካከለኛ ስም	የሶሻል ሴኩሪቲ ቁጥር

አድራሻ	ከተማ/ስቴት	ዚፕ ኮድ	የመንጃ ፈቃድ/መታወቂያ ቁጥር
	Washington, D.C.		

እኔ _____ በመንጃ ፈቃዴ ወይም የመታወቂያ ካርዴ ላይ የጾታ
(ስም ይጻፉ)

ስያሜ እንደሚከተለው እንዲነበብ እፈልጋለሁ፡- (አንዱን ያክብቡ)፡- **ወንድ** **ሴት**

ይህ የጾታ ስያሜ የማግኘት ጥያቄ የመንጃ ፈቃዴ/ የመታወቂያ ካርዴ ትክክለኛ የጾታ ማንነቴን የሚያንጸባርቅ መሆኑን ለማረጋገጥ እንጂ ለሌላ የማጭበርበር ወይም የህገወጥ ዓላማ እንዳልሆነ በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ፊርማ፡- _____ ቀን፡- _____

ክፍል ሁለት፡- በሕክምና ወይም በማህበራዊ አገልግሎት ባለ ሥልጣን የሚሞላ

የአገልግሎት ሰጪ የመጨረሻ ስም	የአገልግሎት ሰጪ የመጀመሪያ ስም	የአገልግሎት ሰጪ ማዕረግ

የአገልግሎት ሰጪ ድርጅት ስም (ተገቢ ከሆነ)

የአገልግሎት ሰጪ አድራሻ	ከተማ	ስቴት	ዚፕ ኮድ

የአገልግሎት ሰጪ ስልክ	የአገልግሎት ሰጪ ኢሜይል	የአገልግሎት ሰጪ ድረጅት ወይም or የሙያ ፈቃድ ቁጥር

እኔ፡-

- ሐኪም
- ፈቃድ ያለኝ ቴራፒስት ወይም አማካሪ
- ጉዳይ አስፈጻሚ ወይም የማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኛ
- ሌላ፤ እባክዎን ይግለጹ፡-

በእኔ ሙያዊ አስተያየት፤ የአመልካች የጾታ ማንነት እንደሚከተለው ነው፡- (አንዱን ያክብቡ)፡- **ወንድ** **ሴት**
እናም እንደዚህ ሆኖ ረዘም ላለ ጊዜ ሊቀጥል እንደሚችል በሚገባ እጠብቃለሁ።

ከላይ ያለው መረጃ እውነተኛ እና ትክክለኛ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ፊርማ፡- _____ ቀን፡- _____

የውሸት ስም ወይም አድራሻ እና / ወይም እያወቁ በዚህ ማመልከቻ ማንኛውም የውሸት ቃል በማድረግ የሚጠቀም ማንኛውም ሰው የዲ.ሲ.ን ሕግ ጥሷል፤ ለዚህም ከ $1,000 በማይበልጥ የገንዘብ ቅጣት ወይም የ180 ቀናት እስራት ወይም በሁለቱንም ቅጣት ይደርስበታል።(D>C. Official Code §22-2405)።

በማንኛውም የዲሲ መንግሥት ኤጀንሲ ወይም ባለስልጣን ብክነትን፣ ማጭበርበርን እና አላግባብ መጠቀምን ሪፖርት ለማድረግ፤ ለዲሲ ኦጠቃላይ ተቆጣጣሪ (DC Inspector General) በስልክ ቁጥር 1-800-521-1639 ይደውሉ። Ver. 11/2006